1. ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ የሠንጠረዥ አይነት ምንነትን እና ምጣኔዎች ይግለጹ?

2. ዶ/ር አበበ በXYZ ካምፓኒ ተቀጥረው የሚሰሩ ሲሆን በወር 23,500 ብር ይከፍላቸዋል ። ዶ/ር አበበ ለመንግስት ምን ያህል ግብር ይከፍላሉ?

3-ማንኛውም ቀጣሪ ተቀጣሪው መክፈል የሚኖርበትን ግብር ከተቀጣሪው ገቢ ላይ ሳይቀንስ ራሱ ለተቀጣሪው በሙሉ ወይም በከፊል የከፈለለት እንደሆነ፣ ግብሩ እንዴት ይሰላል?

4. አቶ አየለ በXYZ ካምፓኒ የድርጅቱ ሲኒየር አካውንታት ሆነው ተቀጥረዋል ። ድርጅቱ በወር 15000 ብር ደመወዝ የሚከፍላቸው ሲሆን በ2013 ዓ.ም ባሳዩት ውጤታማ የስራ አፈጻጸም የ3ወር ደሞወዛቸውን በዓመቱ መጨረሻ በቦነስ መልክ ቢከፍላቸው አቶ አየለ ካገኙት ቦነስ ላይ መክፈል የሚጠበቅባቸው የስራ ግብር ስንት ነው?

5. አቶ አበበ በXYZ ካምፓኒ ድርጅት ተቀጥረው የሚሰሩ ሲሆኑ በድርጅቱ 26 ዓመት አገልግለዋል። 10,500 ብር ደመወዝ ይከፈላቸዋል ። አቶ አበበ በ2013 ዓ.ም ያልተጠቀሙት 20 ቀናት የአመት ፍቃድ በገንዘብ ተቀይሮ እንዲሰጣቸው በጠየቁት መሰረት በመጨረሻው ዓመት ሂሳቡ ተሰልቶ ተሰጣቸው፤

- የአመት ፍቃዳቸው በገንዘብ ተቀይሮ ከተሰጣቸው ገንዘብ ላይ ምን ያህል የስራ ግብር ይከፍላሉ?

6. ዶ/ር ከበደ በYZ ካምፓኒ የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ ሲሆኑ በድርጅቱ በነበራቸው ቆይታ በወር 30,500 ብር ይከፈላቸው ነበር ዶ/ር ከበደ በውላቸው መሰረት 7 አመት ሰርተው ድርጅቱ ከስራ አሰናበታቸው።

- ተሰናባቹ ግለሰብ ከስራ ሲሰናበቱ ስንት ብር ሊከፈላቸው ይገባል?
- ከሚከፈላቸው የስንብት ክፍያ ላይ ስንት ብር ለገቢ ባለስልጣኑ የስራ ግብር መክፈል ይኖርባቸዋል?

7. በወር15,000 ብር ደሞወዝ የሚከፈለው ባለሙያ በሳምንት የዕረፍት ቀን የትርፍ ሰዓት በወር ውስጥ 40 ሰዓት ቢሰራ

የትርፍ ሰዓት ክፍያው ስንት ነው ?

የሚከፈል የስራ ግብር ስንት ይሆናል ?

8. ወ/ሮ አልማዝ የYXZ ጨርቃ ጨርቅ እንጂነሪንግ ኩባንያ ምክትል ሰራ አስኪያጅ ሆነው የሚሰሩ ሲሆን በወር 60ሺህ ብር ደመወዝ ይከፈላቸዋል ። ከዚህ በተጨማሪም የቤት አበል በወር 5ሺህ ብር፣ስልክ ጥሪ ወጪ 200፣ የትራንስፖርት መጓጓዣና መዘዋወሪያ አበል 7500 ብር ፣ ከቤት ወደ ሥራና ከሥራ ወደ ቤት 500 ብር እና ለመስክ ሰራ ለ10 ቀናት ለተንቀሳቀሱበት የውሎ አበል ተከፍሏቸዋል

- ጥያቄ አንድ፡-ታክስ የሚከፈልባቸው ገቢዎች የትኞቹ ናቸው?
- ጥያቄ ሁለት፡-ታክስ የማይከፈልባቸው ገቢዎች የትኞቹ ናቸው?
- ጥያቄ ሦስት፡- ታክሱ ስንት ነው?
- ጥያቄ አራት፡- የተከፈላቸው ውሎ አበል ምን ያህል ነው?
- ጥያቄ አምስት፡- ከታክስ በኋላ የተገኘ ገቢ ስንት ነው

9. ከመቀጠር ከሚገኙ የአይነት ጥቅሞች እና ስለሚከፈል ግብር አስረዱ?

10. እንደ ዓይነት ጥቅሞች የማይቆጠሩትን በጥቂቱ ዘርዝሩ?

11-በውጭ ሀገር ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ምንነትን ይግለጹ?

12. ሠልጣኞች ከመቀጠር ከሚገኙ ገቢ ላይ በገደብ እና ያለ ገደብ ከታክስ ነፃ የተደረጉ ገቢዎችን ይዘርዝሩ?

13. የወጪ መጋራት አከፋፈል ሥርዓትን ያስረዱ